# ውርዬ እና ቡችዬ



ከ
አበበ አለሙ

**ለልጆች የቀረበ መጽሐፍ**

*የመጀመሪያ ዕትም 1998 ዓ.ም.*

## መግቢያ

ልጆች በጥሩ ሥነ-ምግባር ታንፀው እንዲያድጉ ወላጆችና እያንዳንዱ ዜጋ ኃላፊነት አለበት።

የልጆችን አዕምሮ በጥሩ ሁኔታ ለመቅረጽ መፃሕፍት ከፍተኛ ድርሻ አላቸው። ልጆች ከመፃሕፍት ቁም ነገሮችን እንዲቀስሙ መፃሕፍት የማንበብ ፍላጐት እንዲያድርባቸው ማድረግ ይገባል።

ከዚህ በፊት ከፃፍኳቸው 'ብልኋ ቀበሮ' እና 'ብልኋ ሴት' ከተባሉት የተረት መፃሕፍት በተጨማሪ እነሆ ደግሞ አሁን ይህቺን መጽሐፍ ልጆች በቀላሉ አንብበው እንዲረዱ በሥዕላዊ መግለጫ አስደግፌ አቅርቤያለሁ።

ልጆቹም የቀረቡትን ፅሑፎች መረዳት አለመረዳታቸውን ለማረጋገጥ ከእያንዳንዱ ድርሰት መጨረሻ የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲመልሱ ማገዝና ማበረታታት ይገባል።

# ውርዬ እና ቡችዬ

የልጆች መጽሐፍ

ከ
አበበ ዓለሙ

አዲስ አበባ
1996


የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው::
All rights reserved
©Copy right 1996

ሥዕል:- በአበበ ዓለሙ
ኮምፒውተር ጽሑፍ:- በጉልደን ትምህርት ማዕከል

## ማውጫ

ገፅ


- ውርዬ እና ቡችዬ ---------------------------5
- ሚሚዬ እና ዶሮዎቿ -----------------------17
- ንብ እና ዝንብ -----------------------------26
- ድመት እና አይጦች ------------------------35
- ቀበሮ፣ ጠጣ እና የሜዳ አህያ---------------44

## ውርዬ እና ቡችዬ

በአንድ ሀብታም ሰው ቤት የሚኖሩ አንዲት ድመትና አንድ ውሻ ነበሩ:: ከህፃንነት ጊዜያቸው ጀምሮ አብረው ስለአደጉ በጣም ይዋደዱ ነበር:: ድመቷ ውሻውን 'ቡችዬ' እያለች ስትጠራው ውሻው 'ውርዬ' እያለ ነበር የሚጠራት:: አሳዳጊያቸው ብዙ ሳሞች፣ ኮርማዎች፣ በጎች እና ፍየሎች ስላላቸው ሁልጊዜ ውሃና ምግብ ይሰጧቸዋል:: ገላቸውም ሲቆሽሽ በሣሙና ያጥቧቸዋል::

ከዕለታት አንድ ቀን አሳዳጊያቸው በማለዳ ተነስተው ከብቶቹን የሣር ድርቆሽ ሲያበሉ ውርዬ እና ቡቺ በር ላይ ቆመው እየተመለከቱ:-

"ለመሆኑ ጌቶች ትናንትና ራትሽን ሰጡሽ?" ሲል ቡቺ ውርዬን ጠየቃት::

"አልሰጡኝም:: ይሰጡኛል ብዬ እግራቸውን እየታከኩና እየላስኩ ሚያው..... ሚያው ብል እንኳ ዝም አሉኝ:: የታለበውንም ወተት ከቤተሰቦቻቸው ጋር ጠ ጥተው የተረፋቸውን ወተት ማስቀመጫ ዕቃ ውስጥ ገልብጠው ቆለፉት::" ብላ በምሬት መለሰችለት::

"ታዲያ ያምሽን ከምታድሪ ለምን አይጥ አድነሽ አትበይም ነበር?" ሲል በድጋሚ ጠየቃት::

"አይጥ? አይ ቡችዬ! በዛሬው ጊዜ እኮ አይጦቹ ብልጥ ሆነዋል! እንደ ድሮው መሬት ለመሬት መሄድ ትተው ላይ ላዩን በጣራው ሥር መሄድ ጀምረዋል:: ለእኛ እንደ ሰማይ እርቆ የተሰቀለው ቋንጣ ለአይጦቹ ቅርብ ስለሆነ በገመዱ ላይ እንደልባቸው ከወዲያ ወዲህ እየተረማመዱ ጥርቅም አድርገው ይበሉባቸዋል::ጌቶች ግን በእኔ ያሳብባሉ::" አለችው::



"አንተስ ቡችዬ! ትናንት ጌቶች ራትህን ወረወሩልህ?"

"አይ ውርዬ! እኔማ ምግብ ከቀመስኩ ይኸው ዛሬ ሦስተኛ ቀኔ ነው:: ጅራቴን እያወዛወዝኩ ቀን ቀን በር በሩን ላይ እውላለሁ:: ሌሊት ሌሊት ደግሞ ግቢውን ስጠብቅ አድራለሁ:: የትናንቱ አዳሬ ግን አዳር አይምሰልሽ:: ሌቦች ዙሪያውን ከበው ላሞቹንና ፍየሎቹን ሊሰርቁብን ነበር:: ሌሊቱን ሙሉ እንደዚያ ስጮህ ጌቶች እንኳ ብቅ ብለው አላገዙኝም::

የሚገርመው ነገር ደግሞ ከሌቦቹ መካከል አንደኛው ሌባ የጌቶች የራሳቸው የቅርብ ጓደኛ ነው:: ቀን ቀን ከእርሳቸው ጋር እዚህ ቤት እየመጣ ሲጫወት ይውላል:: ያልታየ መስሎታል! ከአሁን በኋላ አልታወቀብኝም ብሎ እንደልማዱ ቀን ቢመጣ አላስገባውም::" አላት::

"ቡችዬ! እስከመቼ ድረስ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ እንኖራለን? እዚህ ተቀምጠን በችጋር ከምናልቅ ወደ ዘመዶቻችን ዘንድ መሄድ አለብን::" ብላ ውርዬ በብስጭት ነገረችው::


"የአንቺ ዘመዶች የት ነው ያሉት?"

“ከዚህ ትንሽ ራቅ ብሎ በሚገኘው ጫካ ውስጥ ነው::”

“ስማቸው ማን ማን ይባላል?”

“አነር፣አበሽማኔ፣ ነብር ይባላሉ::” ነብር የአባቴ ታላቅ ወንድም ሲሆን ለእኔ አጐቴ ነው:: አንተስ ዘመዶች በቅርብ የሉህም?”

“አሉኝ:: የእኔም አጐት የሚኖረው የአንቺ ዘመዶች በሚኖሩበት ጫካ ውስጥ ነው:: ስሙም ጅብ ይባላል:: የአካባቢው ልጆች “አያ ጅቦ” ይሉታል:: ሌሊት ሌሊት ሊጠይቀኝ እዚህ ድረስ ይመጣል::” ሲል መለሰላት::






“አይ ቡችዬ! ይልቁንስ ምኝ አትሁን:: ጌቶች የሚንከባከቡት የራሳቸውን ልጆች፣ የሚያልቧቸውን ላሞች እና ቢሸጧቸው ዋጋ የሚያወጡላቸውን ከርማዎች እንጂ እኛን የቤት ውስጥ አገልጋዮቻቸውን አይደለም:: ስለዚህ ዘመዶቻችን ወደ አሉበት ሥፍራ መሄድ አለብን:: ተነስ! ተነስ! ብላ መከረችው::

ቡቺ በምክሯ ተስማምቶ ከእርሷ ጋር ጉዞውን ቀጠሉ:: ቀኑን ሙሉ ሲጓዙ ውለው አመሻሹ ላይ ዘመዶቻቸው ከሚገኙበት ጫካ ደረሱ:: ጫካው ጥቅጥቅ ያለ በመሆኑ ውርዬ እና ቡቺ ወደ ውስጥ ለመግባት ፈሩ::

“ቡቺዬ! አንተ ታላቅ ስለሆንክ ቀድመህ ግባ እኔ ከኋላህ እከተልሃለሁ::” አለች ውርዬ::

“እኔ አልቀድምም:: ጠላት ቢመጣብን እንኳ ከእኔ ይልቅ አንቺ ቀድመሽ ዛፍ ላይ ወጥተሽ ስለምታመልጪ አንቺ ቅደሚ::” አላት ቡችዬ::

ውርዬም በቡቺ ሀሣብ ተስማምታ ቀደም ቀደም እያለች ወደፊት ስትሄድ ቡችዬ ተከትሏት ጉዟቸውን ቀጠሉ::



ትንሽ እንደተጓዙ አንዲት ከቡችዬ ከፍ የምትል ባለ ትላልቅ ጆሮዎች እንስሳ ከፊት ለፊታቸው መጣች::

“ጤና ይስጥልኝ:: እኔ ድመት እባላለሁ:: እርሱ ደግሞ ውሻ ይባላል:: የመጣነው ከከተማ ሲሆን በዚህ ጫካ ውስጥ የሚኖሩትን ዘመዶቻችንን ለመጠየቅ ስለፈለግን ነው::” ብላ ውርዬ ራሷንና ጓደኛዋን ከአስተዋወቀች በኋላ፡-



“አንቺስ ስምሽ ማን ይባላል? የአካባቢው ነዋሪ ነሽን?”

“አዎን የዚሁ ሠፈር ነዋሪ ነኝ:: ስሜ ጥንቸል ይባላል::”

“የዚህ አካባቢ ነዋሪ ከሆንሽ ጅብና ነብርን አታውቂያቸውም?” ብሎ ቡቺዬ በተራው ጠየቃት::

“አውቃቸዋለሁ:: በሠፈሩ የተከበሩና የተፈሩ ናቸው:: እነርሱን የማያውቅ ያለ አይመስለኝም:: ጅብን አያ ጅቦ እያልን ስንጠራው ነብርን ደግሞ አያ ነብሮ እያልን ነው የምንጠራው:: ትናንትና ሌሊት አያ ጅቦ አንደኛዋን ልጄን በልቶብኛል:: ዛሬ ረፋዱ ላይ ደግሞ አያ ነብሮ ሁለተኛዋን ልጄን በላብኝ:: አሁን ደግሞ እኔን ሊበላኝ ሲል አምልጬ ነው የመጣሁት:: ስለዚህ እናንተም ወደ መጣችሁበት ብትመለሱ ይሻላችኋል::” ብላ ጥንቸል መከረቻቸው::



“እኛ ዘመዶቻቸው ስለሆንን ምንም ነገር አያደርጉንም::” አለ ቡችዬ::

“ሞኞች አትሁኑ! አያ ጅቦና አያ ነብሮ የራሳቸውንም ልጆች የሚበሉ ጨካኝ አውሬዎች ሆነዋል:: ስለዚህ እናንተንም ይበሏችኋል::” ብላ በድጋሚ መከረቻቸው::

“አሳዳሪያችን ከፍተኛ በደል ስለአደረሱብን ተመልሰን አንሄድም:: እዚሁ ዘመዶቻችን የሚያደርጉንን በትዕግሥት እንቀበላለን::” ብላ ውርዬ በምሬት ተናገረች::

“አሳዳጊሽ ምን ዓይነት በደል ቢያደርስብሽ ነው እንደዚህ ምርር ብለሽ የምትናገሪው?” ብላ ጥንቸል ውርዬን ጠየቀቻት::

“ሥጋና ወተት አይሰጡኝም::”

“አንተስ ምን በደል ደርሶብሃል?”


“እኔንም ምግብ ከልክለውኛል:: ሌሊትና ቀን ግቢውን ስለምጠብቅ ሥራ ይበዛብኛል:: በተጨማሪ ግቢውን አቆሸሽክ ይሉኛል::” ብሎ ቡችዬ መለሰላት::

“አንቺንስ አሳዳጊዎችሁ ግቢውን አቆሸሸሻል አላሉሽም?” ብላ ጥንቸል ውርዬን ጠየቀቻት::



“እኔ እንኳ በዚህ አልታማም:: እንኳን የራሴን ቆሻሻ ይቅርና የአሳዳሪዎቼንም ቆሻሻ እኔ ነኝ ቆፍሬ የምቀብርላቸው::” አለቻት::

ይህ የምትነግሩኝ ሁሉ በቂ ምክንያት ስላልሆነ ቤታችሁን ትታችሁ መምጣታችሁ በጣም ያሳዝናል:: ወደ እዚህ ሥፍራ መጥታችሁ ህይወታችሁን ከምታጡ እዚያው ከጌቶቻችሁ ጋር ተቻችላችሁ ብትኖሩ ይሻላችኋል::



ባይሆን እኔ ከጌቶች እግር ላይ ወድቄ አስታርቃችኋለሁ:: አስታራቂ እንግዳ ስለሆንኩኝ እሺ እንደሚሉኝ እርግጠኛ ነኝ። ስለዚህ ኑ ተመለሱ::" ብላ መክራ መለሰቻቸው:: ከዚያም ጥንቸል ለነ ቡቺ በገባችው ቃል መሠረት ወደ ከተማ ጉዟቸውን ጀመሩ::

ሌሊቱን ሙሉ ተጉዘው ሊነጋጋ ሲል ከጌቶች ግቢ ሲደርሱ ጌቶች እንደወትሮው በማለዳ ተነስተው ላሞቻቸውን እያለቡ ነበር።

"እንደምን አደሩ ጌቶች::" አለች ጥንቸል ጎንበስ ብላ::

"እንደምን አደርሽ? የሩቅ ሀገር እንግዳ ዛሬ እቤቴ ድረስ እንዴት መጣሽ? አሉ ጌቶች የወተት ማለቢያቸውን አስቀምጠው::

"ጌቶች! እኔ የመጣሁት ውሻና ድመት እርስዎ ዘንድ ሽምግልና ልከውኝ ነው::" ብላ እግራቸው ላይ ወድቃና ድምጿን አለስልሳ ሁለቱ የደረሰባቸውን ችግር መናገር ስትጀምር ፤

"አንቺ ግን እንዴት ደፍረሽ መጣሽ? በይ ተነሽና ንገሪኝ ለማስታረቅና ለማስማማት የሚመጣ ሁሉ መከበር አለበት::" አሏት::



"አመሰግናለሁ! እኔም ይህንኑ ስላወቅሁ ነው ያለ ፍርሃት የመጣሁት:: ብላ ጥንቸል ትላልቅ ጆሮዎቿን ከወዲያ ወዲህ እያራገበች ውርዬና ቡቺ የነገሯትን ሁሉ ነገረቻቸው::

ሰውዬው በአዘኔታ ራሳቸውን ነቀነቁና "እኔ እንደዚህ እንደተበደሉና እንደተራቡ አላወቅሁም ነበር:: በጣም አዝናለሁ:: ከዛሬ ጀምሮ ለመላው ቤተሰብ ይነገርላቸዋል:: እዚህ ሁሉም እየሠራ መኖር እንዳለበት እያወቀ ነውና እነርሱም በርትተው ይስሩ አንቺንም እናመሰግናለን:: በሉ ውርዬ እና ቡቺ ጥንቸልን ወደ ጓሮ የአትክልት ቦታ ወስዳችሁ ጣፋጩን አረንጓዴ ጎመን ጋብዟት::" ብለው አሰናበቷቸው::

ውርዬ እና ቡቺ በጣም ተደስተውና ሁለቱም አመስግነው ጥንቸልን ወደ ጓሮ ወስደው በሚገባ ጋበዟት::



## ጥያቄ

1. የውርዬና የቡቺ አሳዳጊ ምን ምን ነበሩ-ቸው?
2. ውርዬና ቡችዬ በምን ምክንያት ወደ ዘመዶቻቸው ዘንድ ለመሄድ ፈለጉ?
3. ውርዬ እና ቡቺ በጫካው ውስጥ ሲጓዙ ማንን አገኙ?
4. ጥንቸል ውርዬንና ቡችዬን ወደ አሳዳጊያቸው ለምን መለሰቻቸው?
5. የውርዬና የቡችዬ አሳዳጊ ጥንቸልን እንዴት ተቀበሏት?



# ሚሚዬ እና ዶሮዎቿ

ወላጆቿ ዶሮ በማርባት የሚተዳደሩ ሚሚ የምትባል ልጅ ነበረች:: ወላጆቿ ከሚያረቧቸው ዶሮዎች መካከል አባቷ አንድ ቄብ ዶሮ ሰጧት:: ሚሚ ከትምህርት ቤት ስትመለስ የእንጀራ ፍትፍት፣ ጥራጥሬና ውሃ ትሰጣታለች:: ዶሮዋም የሚሚን ከትምህርት ቤት መምጫ ሰዓት ስለምታውቅ በር ላይ ቆማ ትጠብቃታለች:: የሚሚንም ድምፅ ስትሰማ ሮጣ ወደ እሷ ትሄዳለች:: ሚሚ ዶሮዋን ስለምትንከባከባት ትልቅ ዶሮ ሆና እንቁላሎች ጣለችላት::


ሚሚም ዶሮዋ አስራ ሁለት እንቁላል ስለጣለችላት አስራ ሁለት ጫጩቶች እንደሚኖራት አሰበች::

ዶሮዋም እንቁላሎቿን ጥላ ቁፍ ስትል እንቁላሎቹን አስታቀፈቻት:: ከሃያ አንድ ቀናት በኋላም አስር ጫጩቶች ፈለፈለችላት::

ሚሚ ጫጩቶቿንና እናታቸውን ስለምትንከባከባቸው ዶሮዎቿ በጣም ይወዷት ነበር::

ከዕለታት አንድ ቀን ሚሚ ከትምህርት ቤት ስትመለስ ከእናታቸው ጋር ስምንት ጫጩቶች ብቻ በማግኘቷ ተናዳ እየሮጠች ወደ ቤት ገባችና:-

"እማዬ! እማዬ! ጫጩቶቼን ማን ወሰደብኝ? ብላ እናቷን ጠየቀች።




"ጫጩቶቹን የወሰደብሽ ጭልፊት ነው። ኩኩ ቶሎ ደርሶ ባያስጥልልሽ ኖሮ ሁሉንም ልቅም አድርጎ ይጨርስልሽ ነበር።" አለቻት።



ኩኩ ጉረቤቶቻቸው ያሳደጉት ግዙፍ አውራ ዶሮ ነው። አሳዳጊዎቹ ኩኩ እያሉ ስለሚጠሩት የአካባቢውም ነዋሪዎች ኩኩ እያሉ ይጠሩታል። ኩኩ ስሙን ስለሚያውቅ ሲጠሩት እየሮጠ ይሄዳል።

ኩኩ መልኩ ነጭ ሲሆን ኩክኒው ዝርዝርና ቀይ ነው። አንገቱና ክንፎቹ ላይ ጥቁር ጣል ጣል ያደረገበት ሲሆን ቁመቱም ዘለግ ያለ በመሆኑ ከነሚሚ ዶሮዎች መካከል ረዘም ብሎ ይታያል።



እነ ሚሚ ግቢ ያሉት ዶሮዎች አብዛኛዎቹ ኩኩን ይመስላሉ:: ኩኩም መሬት እየጫረ የሚበላ ነገር ሲያገኝ በአፉ እየሰባበረ ልክ እንደአባት የሚሚን ጫጩቶች ይመግባቸዋል::

ጭልፊት ጫጩቶቹን ሊወስድ ሲመጣ የማስጠ ንቀቂያ ድምፅ እያሰማ ጫጩቶቹ አጥር ሥር እንዲደበቁ ከአደረገ በኋላ ጭልፊቱን ያባርርላቸዋል::


ሚሚ ጫጩቶቿን ኩኩ ስለሚጠብቅላት ያለ ስጋት ትምህርቷን መከታተል ጀመረች:: ጫጩቶቹም በጥሩ ሁኔታ አደጉላት::

ሚሚ አዲስ ልብስና ጫማ መግዛት ስለፈለገች ከዶሮዎቹ መካከል ሦስቱን ሸጣ ከገበያ ስትመለስ የዶሮዎቿ እናት እግሯ በቀጭን ገመድ ከአልጋ እግር ጋር ታስሮ በመድረሷ ዶሮዋ ለምን እንደታሰረች አባቷን ጠየቀቻቸው:: አባቷም፤

"ዶሮዋ ዛሬ ምሽት ላይ ትታረዳለች::" አሏት:: ሚሚ በጣም አዝና ዓይኗ እንባ ከተረ::

ኩኩ ዶሮዋን ግቢው ውስጥ ፈልጐ ስለ አጣት እቤት ውስጥ ሊያያት ገባ:: ጓደኛውም ከአልጋ እግር ጋር ጓዳ ውስጥ ታስራ አገኛት::





"ምን አጥፍተሽ ነው የታሰርሽው?"

"የአጠፋሁት ነገር ስለ አለ ሳይሆን ዛሬ ምሽት ሊያርዱኝ ስለፈለጉ ነው:: ቢለዋ ሲስሉ አይቻለሁ:: ልጆቼን ተንከባክበህና ከጠላት ጠብቀህ ስለ አሳደክልኝ በጣም አመሰግናለሁ:: የቀሩትንም አደራ ለአንተ ሰጥቼሀለሁ" አለችው::

ኩኩ በጣም አዘነ:: ትንሽ ካሰበ በኋላ:-

"ተያይዘን ሠፈሩን ለቀን እንጥፋ::" ብሎ መከራት::

" እንዳየኸው እግሬ በገመድ ከአልጋው እግር ጋር ስለታሰረ ማምለጥ አልችልም::" አለችው::

ኩኩ ከአልጋው እግር ላይ የታሰረውን ጫፍ እየሳበ በጥንቃቄ ከፈታላት በኋላ ዶሮዋ ገመዱን እየጐተተች ከኩኩ ጋር ተደብቀው ግቢውን ለቀው ወጡ:: ከዚያም ከግቢያቸው አጠገብ ካለ ትልቅ ዛፍ ላይ ወጥተው ተደበቁ::

የሚሚ ወላጆች ዶሮዋን ከታሰረችበት ስፍራ ሲያጧት ተናደዱ::

"ፈትታ የለቀቀቻት ሚሚ ራሷ ናት::" አሉ::

ሚሚ ከጓደኞቿ ጋር ስትጫወት ቆይታ ወደ ቤቷ ስትገባ:-

"ማን አዞሽ ነው ዶሮዋን ከታሰረችበት የፈታሻት?" ብለው እናቷ በጥያቄና በማስፈራራት አስጨነቋት::

"እኔ አልፈታኋትም.... እኔ አልፈታኋትም..." እያለች አለቀሰች::



"በይ አሁኑኑ አገባሽበት ገብተሽ ከምታመጪበት አምጫት::" ብለው እናቷ አዘዟት::

ሚሚ እንባዋን እየጠራረገች ፍለጋ ወጣች::

የእነ ሚሚ ጐረቤቶች ደግሞ ኩኩን ፍለጋ እነ ሚሚ ቤት መጡ::


"ኩኩን አላያችሁትም? ዛሬ ምሽት እናርደዋለን ብለን ነበር:: እንደወትሮው ልናገኘው አልቻልንም::" አሉ::

"ዛሬ ማታ እንድትታረድ ብለን ከአሰርናት ዶሮ ጋር አብረው ነበሩ:: ሚሚ ዶሮዋን ከታሰረችበት ፈትታ ስትለቃት አብረው የት እንደደረሱ አጣናቸው::" ብለው የሚሚ እናት መለሱላቸው::

የኩኩ ባለቤቶችም ፍለጋ ቀጠሉ:: የሚሚ ዶሮም ሆነች ኩኩ በአካባቢው ሊገኙ አልቻሉም:: ሌባ ሰርቋቸው ሊሆን ይችላል ብለው ስለገመቱ በምትካቸው ሌላ ዶሮ አረዱ::

በማግስቱ ረፋዱ ላይ ኩኩ እነ ሚሚ ግቢ ውስጥ ጥሪ ሲለቅም ታየ:: ሚሚ በኩኩ መገኘት ደስ ብትሰኝም በዶሮዋ መጥፋት ግን አዝና ስለነበር ፍለጋዋን ቀጠለች:: ዶሮዋንም ከግቢያቸው አቅራቢያ ካለው ዛፍ ላይ እግሯ

በገመድ ታስሮና ክንፏ ተንዘርፎ ወደ ታች ተንጠልጥላ አየቻት።






ሚሚም ዛፉ ላይ በጥንቃቄ ወጥታ ገመዱን ከእግሯ ላይ ከፈታችላት በኋላ እናትና አባቷ ምን እንደሚሏት በስጋት እያሰበች ዶሮዋን አቅፋ ወደ ቤቷ ተመለሰች።

"ለአንቺ እና ለኩኩ የተሳለው ቢላዋ ለሌሎች ሆነ።" አለቻት።

## ጥያቄ

1. ለሚሚ ዶሮ ማን ሰጧት?
2. ዶሮዋ ስንት እንቁላል ጣለችላት?
3. ስንት ጫጩቶችስ ተፈለፈሉላት?
4. የሚሚ ዶሮ ለምን ከአልጋ እግር ጋር ታሰረች?
5. ሚሚ የጠፋችውን ዶሮ ከየት አገኘቻት?



# ንብ እና ዝንብ

አንዲት ሠራተኛ ንብ እና አንዲት የቤት ዝንብ በአንድ የቆሸሸ ጠረጴዛ ላይ ተገናኙ።

“ምን ልትሰሪ መጣሽ?” ብላ ዝንብ ንቢቱን ጠየቀቻት።

“የፈሰሰ ሻይ ፍለጋ።”

“የፈሰሰ ሻይ ከምትጠጪ ለምን በእናንተ ሠፈር ከሚወርደው የወንዝ ውሃ አትጠጪም?”

“ውሃ ሲጠማኝ ከወንዝ ውሃ እጠጣለሁ። እዚህ የመጣሁት ግን ሻይ ውስጥ ያለውን ስኳር ፈልጌ ነው።”

“ስኳር ምን ያደርግልሻል?”

“ማር እሠራበታለሁ።”


“ማሩን ሠርተሽ ምን ታደርጊዋለሽ?”



“ለምግብነት እጠቀምበታለሁ የተረፈኝን ደግሞ ገበያ አውጥቼ እሸጠዋለሁ።” አለቻት ንቢቱ።

“ማር እንዴት እንደሚሠራ ልታሳይኝ ትችያለሽ?”

“ላሳይሽ እችላለሁ። ነገር ግን ማር በአንድ ንብ ብቻ የሚሠራ ሳይሆን ብዙ ሺህ ንቦች በህብረት የሚያመርቱት የጋራ ጥረት ውጤት ነው።” ብላ ገለፀችላት።



ዝንብ የንቦቹን የሥራ እንቅስቃሴ ለማየት ጓጉታ ስለነበር ከንቢቱ ጋር ወደ ንቦቹ ቀፎ ገባች:: በቀፎው ውስጥ በመሠራት ላይ ያለውን የማር እንጀራ፣ የንቦቹን የሥራ ትጋት፣ እንዲሁም የንቦቹን ንግሥትና ድንጉላ ንቦች ተዘዋውራ ከተመለከተች በኋላ ወደ ቤቷ ተመለሰች::

ንቦች በህብረት ተደራጅተው በመሥራታቸው ለዚህ ጥሩ ውጤት ስለበቁ እኔም ዝንቦችን አደራጅቼ መርዝ ማምረት መጀመር አለብኝ:: እኔም የዝንቦቹ ንግሥት እሆናለሁ ብላ አሰበች:: በሰፈሩ ቆሻሻ ሥፍራ የሚገኙትን ብዙ ሺህ ዝንቦች ጠርታና አስጠርታ በአንድ ሽንት ቤት ውስጥ እንዲሰበሰቡ አደረገች::

ሌሎች ዝንቦችም ከየአለቡት ሥፍራ ተጠራርተው በቦታው ላይ ተገኙ::

"የተከበራችሁ ዝንቦች:: ዛሬ እዚህ እንድትሰበሰቡ የአደረኩበት ዋና ምክንያት ከእኛ በቁጥር የሚያንሱ ንቦች በአንዲት ንግሥት ተደራጅተው ከፍተኛ ገቢ ሊያስገኝላቸው የሚችል ማር በአንዲት ትንሽ ቀፎ ውስጥ በህብረት እያመረቱ ነው:: እኛም እንደ እነርሱ በአንድ ላይ ተደራጅተን ብንሠራ ችሎታችንና አቅማችን የፈቀደልንን ያህል መርዝ ማምረት እንችላለን::"



በማለት ሰብሳቢዋ ዝንብ ስትናገር ተሰብሳቢዎቹ ዝንቦች ደስታቸውን በጭብጨባ ገለፁ:: ሰብሳቢዋንም የዝንቦቹ ንግሥት አድርገው ሾሟት::

"ሁላችሁም ከአሁኑ ሰዓት ጀምሮ ለመርዝ ማምረቻ የሚያስፈልገንን ሁሉ ይዛችሁ እንድትመጡ::" ብላ አዘዘቻቸው::

ከተሰብሳቢዎቹ መካከል አንደኛዋ እጇን አውጥታ:-

"መርዝ ብናመርት ማን ይገዛናል? ማምረት ያለብን እኛም እንደንቦቹ ማር ነው::" ብላ ሀሳቧን አቀረበች::

"አንድን ምርት ለማምረት ፍላጎት ብቻ ሳይሆን ችሎታ እና አቅም አስፈላጊ ነው:: በተጨማሪ ደግሞ የእኛ ምርት ለየት ያለ መሆን አለበት ስለሆነም፣ እኛ ማምረት ያለብን መርዝ እንጂ ማር አይደለም:: በዛሬው ጊዜ ገበያ ላይ ወጥቶ የማይሸጥ ነገር የለም:: ይኽ አያሳስበንም:: ይልቁንስ ጊዜ ሳናጠፋ ፈጥነን ወደ ሥራችን እንሂድ::" በማለት ንግሥቲቱ ዝንብ መለሰችላት::

ዝንቦቹም በየፊናቸው ተሠማርተው በአጭር ጊዜ ውስጥ ተሰብስበውበት በነበረው ሽንት ቤት ውስጥ ብዙ መርዝ አመረቱ::



የተመረተውንም መርዝ ንግሥቲቱ ዝንብ ወደ ገበያ ይዛ ወጣች:: ከገበያተኞቹ መካከል ያቺን ሠራተኛዋን ንብ ማር ተሸክማ አገኘቻት::



“ምን ልትሸጪ መጣሽ?” ብላ ንቢቱ ዝንቢቱን ጠየቀቻት::

“መርዝ::”

“መርዝ ለምን የሚጠቅም ነው?”

“ማንኛውንም ህይወት ያለውን ነገር ለምሳሌ ትኋንን፣ ቁንጫን፣ በረሮን እና የመሣሠሉትን ሁሉ ለመግደልም ሆነ ለማሳመም የሚጠቅም መድሃኒት ነው::” ብላ ንግሥቲቱ ዝንብ መለሰችላት::

“ታዲያ ይህን ገዳይ መድሃኒት ስትሠሪ አንቺ እንዴት አልሞትሽም?”

“መርዙ የሚገድለው ያመረተውን ሳይሆን የተመገበውን ሁሉ ነው::” አለቻት::

“ይህንንስ የሚገዛሽ ያለ አይመስለኝም:: መርዝ ከምታመርቺ ማር ብታመርቺ ብዙ ገዢ ታገኚ ነበር:: ለማንኛውም የዕድልሽን ሞክሪ::” አለች ንቢቱ::

ዝንቧ መርዙን ንቢቱ ደግሞ ማሩን ሊሸጡ ከገበያው መሃል ጉን ለጉን ተቀመጡ::

“ንብ ጣፋጭ ማር ፈላጊ! ወለላ ማር ፈላጊ! ስትል ዝንብ በበኩሏ መርዝ ፈላጊ!...ፍቱን መርዝ ፈላጊ! እያሉ ለገበያተኛው ማስተዋወቅ ጀመሩ::

ብዙ ገበያተኞች የማሩን ጣፋጭነት ለማወቅ እየቀመሱ ከመሄድ በስተቀር ማሩን የሚገዛ አልነበረም:: ነገር ግን ዝንብ ያመጣችው መርዝ ወዲያውኑ ተሸጦ አለቀ::

ይህን ያየችው ንብ "የእኔ ማር ቀጭ ብሎ የአንቺ መርዝ ተሸጦ አለቀ:: የሚገርም ነው:: ማሩ አልተሸጠም ብዬ ብመለስ ንግሥቲቱ እውነት አይመስላትም:: አታምነኝም:: በወታደሮቿም ታስገድለኛለች:: ምን እንዳደርግ ትመክሪኛለሽ? በማለት ስጋቷን ነገረቻት::

"አንቺ የዋህ ነጋዴ ነሽ:: በንግድ ሥራ እንደ አንቺ ያለ የዋህ ነጋዴ ሽጦም ሆነ አትርፎ አይገባም:: ስለዚህ የያዝሺውን ማር ነው ከማለት ይልቅ መርዝ ነው ብለሽ ሽጭው::" ብላ መከረቻት::

ንብም የዝንብን ምክር ተቀብላ፣

"መርዝ ፈላጊ! .... ፍቱን መርዝ ፈላጊ! ...." ማለት ጀመረች:: የያዘችውንም ማር መርዝ ነው ብላ ሸጣ ጨረሰች::

"ከእንግዲህ ወዲህ ንቦች መርዝ እንጂ ማር ማምረት የለባችሁም:: ብላ ዝንብ መከረቻት::



ንብ በዝንብ ሀሣብ ተስማምታና በገበያ ላይ ያጋጠማትን ችግር ለንግሥቲቱ በዝርዝር አስረድታ ከአሁኑ ሰዓት ጀምሮ መርዝ እንጂ ማር ማምረት እንደሌለባቸው ሃሣብ አቀረበች::

ንግሥቲቱ በቀረበው ሀሣብ በመስማማቷ ንቦቹ በቀፎው ውስጥ እንዲሰበሰቡ አደረገች:: ከዚያም ማር ገዢ ስለአጣ ከአሁኑ ሰዓት ጀምሮ ለመርዝ መሥሪያ የሚያገለግለውን ቅመም ከተለያዩ ጣፋጭ መዓዛ ካላቸው አበቦች ሳይሆን በየቦታው ከተጠራቀመው ቆሻሻ ላይ ሊያገኙ እንደሚችሉ ነገረቻቸው::

ንቦቹ በተሰጣቸው ትዕዛዝ መሠረት በየቆሻሻው ላይ ሲያርፉ አብዛኞቹ ንቦች ወዲያውኑ በፀና ታመሙ:: አንዳንዶቹም ሞቱ::

በቀፎው ውስጥ የቀሩት ንቦች በጓደኞቻቸው መታመምና በአንዳንዶቹም ላይ በደረሰው የሞት አደጋ ምክንያት ተደናግጠው እንደገና በመሰብሰብ:-

ዝንብ ባቀረበችው ምክርና ሐሳብ ላይ በስፋት ተወያዩ:: ከንቦቹ መካል ብዙ ዕውቀትና ልምድ የነበረው ንብ ተነስቶ:-

"እኛ በተፈጥሮአችን መልካም ነገር አምርተን ማቅረብ እንጂ ሌሎችን የሚጨርስና ጉዳት ላይ

የሚጥል ነገር መሥራት የእኛ የተፈጥሮ ሙያና ሥራ አይደለም። ጥሩ ስምና ሙያችን በጊዚያዊ ጥቅም መበላሸት የለበትም።” አለ።

“እኔም ይህን ሐሳብ እደግፋለሁ።” አለ አንድ ወጣት ንብ።

“ዝንቦችም ሆኑ ሌሎች በራሪዎች መርዝ የሚሠሩት በተፈጥሯቸውና በሙያቸው ማር መሥራት ስለማይችሉ ነው። ስለዚህ እኛ ምን ጊዜም ቢሆን ጥሩና ጠቃሚ ነገር መሥራት አለብን።” አለ አንድ ሌላ በአስተዋይነቱ የታወቀ ንብ።

በመጨረሻም ንቦቹ ሁሉ፡-

“ከአሁን በኋላ ለገንዘብ ብለን ሳይሆን አቅማችን፣ሙያና ችሎታችን በሚፈቅድልን መሠረት ማር ማምረት አለብን።” ብለው ወሰኑ።

### ጥያቄ

1. ዝንብና ንብ ለመጀመሪያ ጊዜ የት ተገናኙ?
2. ዝንብ ወደንቦች ቀፎ ለምን ገባች?
3. ዝንብና ንብ ምን ምን ሊሸጡ ወደ ገበያ ሄዱ?
4. ንቦቹ በምን ምክንያት ታመሙ ወይም ሞቱ?
5. ንቦቹ በመጨረሻ ምን ለማምረት ተስማሙ?





## ድመት እና አይጦች


በአንድ ጉድጓድ ውስጥ ከስድስት የልጅ ልጆቻቸው ጋር የሚኖሩ አንድ ሽማግሌ አይጥ ነበሩ። ሽማግሌው አይጥ እናትና አባታቸው በሌሉበት ጊዜ የልጅ ልጆቻቸውን በጉድጓዳቸው ውስጥ ሰበሰቡና፡-

“ልጆቼ! እነሆ እስከ ዛሬ ድረስ በሽማግሌ አቅም ተሯሩጬ ለዚህ ደረጃ አብቅቻችኋለሁ። ከአሁን በኋላ ግን ጉልበቴ ስለደከመ እኔን ልትጦሩኝ ይገባል። ስለዚህ ሁላችሁም ከጉድጓድ ወጥታችሁ ለእኔና ለእናንተ የሚሆን ምግብ ይዛችሁ መምጣት ይኖርባችኋል።” በማለት አያታቸው ነገሯቸው።

ልጆቹም የአያታቸውን ቃል አክብረው ምግብ ለማምጣት ድመት በአካባቢው መኖር አለመኖሯን

እንዲሰልል አንድ ወንድማቸውን ላኩት:: ነገር ግን ከጉድጓድ ወጥቶ ሳይመለስ ቀረ::

አይጦቹም የላኩት ወንድማቸው እንደወጣ መቅረት ስለ አሳሰባቸው አንድ ሌላ ወንድማቸውን ደግሞ እንዲፈልገው ላኩት:: እርሱም ከጉድጓዱ ትንሽ ራቅ ብሎ ዙሪያውን ሲመለከት በመጀመሪያ የተላከውን ወንድሙን ድመት ሲበላው ተመልክቶ በፍጥነት ተመለሰና ሁኔታውን ለወንድሞቹ ነገራቸው:: ወንድሞቹም በጣም አዘኑ::



ምን ማድረግ አለብን ብለው ከተመካከሩ በኋላ ድመት በአካባቢው መኖር አለመኖሯን አረጋግጦ ምግብ




እንዲያመጣላቸው አንድ ሌላ ወንድማቸውን ደግሞ ላኩት::

እርሱም በአካባቢው ድመት አለመኖሯን ካረጋገጠ በኋላ ፍለጋውን ቀጠለ:: ነገር ግን እሱም በተራው እንደወጣ ሳይመለስ ቀረ:: አሁንም እንደገና አንድ ወንድማቸውን እንዲፈልገው ላኩት:: እሱም የጠፋ ወንድሙን ከአንድ ሣጥን ሥር ተኝቶ አገኘው::

“ተነስ! ተነስ! እንሂድ:: ወንድሞቻችን እየጠበቁን ነው::” አለው:: ነገር ግን ምንም መልስ አልመለሰለትም:: ጠጋ ብሎ ወንድሙን በእጆቹ ሲያገላብጠው አጠገቡ የነበረውን መርዝ የተቀባ ዳቦ በልቶ እንደሞተ ስለተረዳ ወዲያውኑ እየሮጠ ወደ ጉድጓዱ ገባና፣

“ወይኔ! ወይኔ! ወንድማችን መርዝ በልቶ ሞቷል!” ብሎ አረዳቸው::

ወንድሞቹም በጣም አዘኑ:: “ቀንደኛ ጠላታችን ድመት ናት:: ይሁን እንጂ ሰዎችም በየሥርቻው የሚያስቀምጡትን ማንኛውንም ዓይነት ምግብ መብላት የለብንም::” ብለው ወሰኑ::



በህይወት ከተረፉት ወንድማማቾች መካከል እንደገና አንደኛውን ወንድማቸውን በአካባቢው ድመት አለመኖሯን አረጋግጦና መሬት ላይ የወደቀ ምግብ ሳይበላ ከሌማቱ ውስጥ ያገኘውን ምግብ ብቻ ይዞ እንዲመጣ ላኩት::

እርሱም ከጉድጓዱ በጥንቃቄ ወጥቶ ቀስ ብሎ ወደፊት ተራመደ:: በአካባቢው ድመት አለመኖሯን ከአረጋገጠ በኋላ መሬት ላይ የወደቁትን ምግቦች እየዘለለ ወደ ሌማቱ ተጠጋ::

ጉድጓዱ ውስጥ የቀሩት ወንድሞቹ በወንድማቸው ጠ ንቃቃነትና ብልሃት ስለሚተማመኑ ምግብ ይዞላቸው እንደሚመጣ በጣም እርግጠኞች ነበሩ::



ነገር ግን እርሱም በተራው ሳይመለስ ቀረ:: የወንድማቸው መቅረት ያሳሰባቸው አይጦች አንድ ወንድማቸው ደግሞ እንዲፈልገው ላኩት::

እርሱም በአካባቢው ድመት አለመኖሯን አረጋግጦ ፍለጋውን ቀጠለ:: የጠፋ ወንድሙን ግን ሊያገኘው አልቻለም:: ባዶ እጁን ከሚመለስ በሌማቱ ውስጥ ካለው እንጀራ ለወንድሞቹ ይዞ ለመሄድ ወሰነ:: እርሱም ሌማቱ ወደ ተቀመጠበት ሣጥን ሥር ሲገባ ወንድሙን በወጥመድ ተይዞ አየው::

ማጅራቱ ላይ የወጥመድ ብረት አርፎበት ዓይኖቹ ፈጥጠው፣ ጥርሶቹ ገጠው፣ ከአፉና ከአፍንጫውም ደም ፈሶት ተመለከተ:: የወንድሙን መሞት ከአረጋገጠ በኋላ ሮጦ ወደ ጉድጓዱ ገባ::

"ወንድማችን በወጥመድ ተይዞ ሞቷል::" ብሎ አረዳቸው:: እነርሱም በጣም አዘኑ:: በጉድጓዳቸውም ውስጥ ሣር ጎዝጉዘው ሀዘን ተቀመጡ::

አያትየው ከጓደኞቻቸው ጋር ሲጫወቱ ቆይተው ወደ ጉድጓዳቸው ሲመለሱ የልጅ ልጆቻቸው በወንድሞቻቸው ሞት አዝነው እያለቀሱ አገኟቸው::

እነርሱም አንደኛው ወንድማቸው በድመት መበላቱን፣ ሁለተኛው መርዝ በልቶ መሞቱንና ሦስተኛው በወጥመድ መገደሉን ነገሯቸው:: አያታቸውም በሁኔታው በጣም አዝነው የቀሩትን በማፅናናት:-

"ወላጆቻችሁ የሞቱት በድመት ተበልተው ነው:: ድመት የእኛ ደመኛ ጠላታችን ናት:: ስለዚህ እሷን ተባብረን መግደል አለብን::" ብለው በቁጭት ተናገሩ::

"ድመት ፈጣንና ከእኛ የተሻለ ጉልበት ስለአላት እሷን መግደል የሚቻል አይመስለኝም:: በዚህ ላይ ዓይኖቿ በጭለማ ውስጥ የማየት ኃይል አላቸው::" አለ ከወንድማማቾቹ አንዱ::

"እውነት ነው:: በእኛ አቅም ድመትን መግደል የሚቻል አይደለም:: የእኛም የወደፊት ዕጣ ፈንታ በድመት መበላት ብቻ ነው::" አለ ሌላኛው ወንድማቸው::

"ልጆቼ! እኔ ወላጆቻችሁንና እናንተን ያሳደኩት የድመቶችንና የሰዎችን አደገኛ መሰናክሎች ሁሉ በማለፍ ነው:: አሁን ግን ዕድሜዬ ስለገፋ እነኝህን



ወጥመዶች ማለፍ አልችልም:: እናንተ ግን ከእኔ ስለምትሻሉ አንድ ዘዴ ልንገራችሁ::

በመርዝ የሞተውን የወንድማችሁን አስከሬን ከወደቀበት ሥፍራ አንስታችሁ ድመቷ አዘውትራ ከምትቀመጥበት ሥፍራ አኑሩትና ኑ::" ብለው አዘዟቸው::


ወንድማማቾቹም የአያታቸውን ትዕዛዝ ተቀብለው ድመቷ የት እንዳለች እንዲያጣራላቸው አንድ ወንድማቸውን ላኩት:: እሷም ከቤቱ ባለቤት ጋር አልጋ ላይ ተኝታ ስታንኮራፋ አይቷት ተመለሰ::

ወንድማማቾቹም ፈጥነው ከጉድጓዳቸው በመውጣት በመርዝ የሞተውን የወንድማቸውን አስከሬን ከወደቀበት ሥፍራ ተሸክመው ሲጓዙ ድመቷ ከእንቅልፏ ነቅታ ከተኛችበት አልጋ ላይ ዘላ ስትወርድ የተመለከቱት አይጦች የወንድማቸውን አስከሬን በድንጋጤ ጥለው እየሮጡ ወደ ጉድጓዳቸው ገቡ::

ድመቲቱም በጣም እርቧት ስለነበር የወደቀውን አስከሬን ጥርቅም አድርጋ ከበላች በኋላ አፏን በእጆቿ እያባበሰች:-

“ዛሬ ብታመልጡኝ ነገ አገኛችኋለሁ፣ እናንተንም እንድባንድ እንደዚህ ቁርጭምጭም አድርጌ እበላችኋለሁ!” ብላ ዛተችባቸው:: ነገር ግን የተመረዘውን አይጥ የበላችው ያቺ ድመት ወዲያውኑ በኃይለኛ የሆድ ቁርጠት አጣደፋት:: በመጨረሻም ሳትውልና ሳታድር ተሰቃይታ ሞተች::

በጉድጓዳቸው ውስጥ የነበሩት ዓይጦችም መሞቷን እንዳወቁ ቀንደኛ ጠላታቸውን በመግደላቸው በጣም ተደሰቱ::





ከጉድጓዳቸውም ወጥተው ደስታቸውን በጅራት ማቆም ጭፈራ ገለፁ:: ከአያታቸው ጋር እየተሯሯጡ ሣጥን ላይ ከተቀመጠው ሌማት ውስጥ ከብዙ ጊዜ በፊት በተቀደደ ቀዳዳ በመግባት እንጀራውን ጥርቅም አድርገው በልተውና የተረፈውን ተሸክመው ወደ ጉድጓዳቸው ገቡ::

“ልጆቼ! ትዕግስት መራራ ናት:: ፍሬዋ ግን ጣፋጭ ነው::”

**ጥያቄ**

1 አይጦቹ የት ይኖሩ ነበር?
2 ወንድማማቾቹ አይጦች በምን በምን ምክንያት ሞቱ?
3. ድመቷ በአይጦቹ ላይ ምን ብላ ዛተችባቸው?
4. ድመቷ እንዴት ሞተች?
5. አይጦቹ ለምን ጨፈሩ?

# ቀበሮ፣ ጠጣ እና የሜዳ አህያ

በአንድ ትንሽ ጫካ ውስጥ የሚኖሩ ቀበሮ፣ ጠጣ እና የሜዳ አህያ ነበሩ:: በጫካው ውስጥ ጅቦች ስለሚያሳድዷቸው ራቅ ወደ አለ ሥፍራ ሄደው ለመኖር ፈለጉ::

"እኔና ጠጣ ከአንተ እኩል ረጅም መንገድ ለመሄድ አቅም ስለሌለን አንተ ብቻህን ሂድ::" አለች ቀበሮ::

"እውነት ነው:: የእግሬ ቆዳ ስስ ስለሆነ እሾህ ሊወጋኝ ይችላል:: ከሜዳ አህያ እኩል ቶሎ ቶሎ መሄድ ስለማልችል እሱ ብቻውን ይሂድ::" አለች ጠጣ የቀበሮን ሃሳብ በመደገፍ::

"እናንተን ትቼ ብቻዬን መሄድ አልፈልግም:: የምታዘግሙም ከሆነ ከእናንተው ጋር አብሬ አዘግማለሁ::" አለ የሜዳ አህያ::

"አንተ ጠንካራ ስለሆንክ እኔ እና ጠጣ በጀርባህ ላይ ተቀምጠን አብረንህ እንሄድ ነበር::" ብላ ቀበሮ አዲስ ሃሣብ አቀረበች::



የሜዳ አህያ በቀበሮ ሀሣብ ተስማምቶ ጠጣንና ቀበሮን በጀርባው ተሸክሞ ጉዟቸውን ቀጠሉ::

በጉዞ ላይ እንዳሉ:-

"አንቺ አንድ ጊዜ ውረጂና እኔ የሜዳ አህያን ልጋልበው::" ብላ ቀበሮ ጠጣን ለመነቻት::

"አንቺ ውረጂ እንጂ እኔ አልወርድም:: እኔም መጋለብ እፈልጋለሁ:: ውረጂ!" አለቻት:: ውረጂ! አልወርድም! እየተባባሉ ሲጨቃጨቁ ከቆዩ በኋላ ቀበሮ በንዴት ጠጣን ወርውራ መሬት ላይ ጣለቻት:: ጠጣ ስትወድቅ አንድ እግሯ በመሰበሩና መራመድ ባለመቻሏ አለቀሰች:: ቀበሮ፣ ጠጣ በመሰበሯ ብትደሰትም የሜዳ አህያ ግን በጣም አዝኖ ነበር::


"ጠጣ በእግሯ መሄድ ስለማትችል በእኔ ጀርባ ላይ ሆና ትሂድ:: ቀበሮ ግን ጤነኛ ስለሆንሽ ከኋላ ከኋላችን ተከተይን::" አለ የሜዳ አህያ::

ቀበሮ ደስተኛ ባትሆንም ጠጣን ደግፋት ከሜዳ አህያ ጀርባ ላይ አስቀመጠቻትና ከኋላ መከተል ጀመረች::

ቀበሮ ብዙ በመጓዟ ምክንያት በጣም ስለደከማት ጦጣን አውርዳ እራሷ ለመቀመጥ ፈለገች:: ትንሽ ከአሰበች በኋላ አንድ ዘዴ መጣላት::


የሜዳ አህያ ጉያው ሥር ሲነኩት እንደሚዘል ስለምታውቅ ጦጣን አሽቀንጥሮ እንዲጥላት ፈልጋ ወደ ሜዳ አህያው ጉያ ገብታ በጥርሶቿ ሆዱን ነከሰችው::

የሜዳ አህያው ጅብ የመጣበት መስሎት ለመከላከል በድንጋጤ ዘሎ በኋላ እግሮቹ በኃይል ሲራገጥ ቀበሮን ደረቷ ላይ መታትና ከመንገድ ዳር ተዘረረች::






ነገር ግን ጦጣ የሜዳ አህያውን አንገት አጥብቃ በመያዟ አልወደቀችም ነበር::



የሜዳ አህያውና ጦጣ በቀበሮ ድርጊት ተናደው ስለነበር እዚያው እተዘረረችበት ቦታ ላይ ትተዋት ጉዞአቸውን ቀጠሉ:: ጦጣ የሜዳ አህያውን ትንሽ እንደጋለበችው:-

“ቁም! ቁም!” አላቸው አንድ የተራበ አንበሳ መንገድ ዳር ካለ ዛፍ ሥር ተነስቶ::

ጦጣና የሜዳ አህያ የአንበሳ ድምፅ መሆኑን ስለአወቁ ደንግጠው ቆሙ::



"እንኳን ደህና መጣችሁ::" አለ አፉን በኃይል ከፍቶ እያገሳ::

ጦጣ ከሜዳ አህያው ጀርባ ወርዳ፣


"እንኳን ደህና ቆየሽኝ:: ክቡር አንበሳ ዛሬ በጣም እንደራበህ ስለአወቅሁኝ ይህን ወደል የሜዳ አህያ ይገፎልህ መጥቻለሁ::" አለችው::

"ውሸቷን ነው! አታላይናት! እኔ ነኝ በጀርባዬ ላይ ይዣት የመጣሁት:: አንተም አይተሃል::



ጠጣን ብላት! ጠጣን ብላት!" አለ የሜዳ አህያ በፍርሃት እየተርበደበደ::


ጦጣ ቀስ ብላ የሜዳ አህያውን ሆድ በጣቶቿ ስትኰጠው በድንጋጤ ዘለለና አንበሳውን ደረቱ ላይ በኃይል እረግጦ ፈረጠጠ:: አንበሳም ሊያመልጠኝ ነው ብሎ ተከተለው::



ጦጣ ግን እያነከሰች ወደ መጣችበት ስትመለስ ከወደ ኋላዋ የሚከተላት መኖር አለመኖሩን እየተገላመጠች ብትመለከት ምንም የሚከተላት እንደሌለ አወቀችና ተረጋግታ ጉዞዋን ቀጠለች:: ብዙ ከተጓዘች በኋላ ቀበሮ ወድቃ ከተኛችበት ሥፍራ ደረሰች::

ጠጣ ከሜዳ አህያ ጋር ስትጓዝ የተራበ አንበሳ እንዳጋጠማቸውና እንዴት አምልጣ እንደመጣች በዝርዝር ለቀበሮ ነገረቻት፡፡ ቀበሮም እነርሱን ተከትላ ሄዳ ቢሆን ኖሮ የሜዳ አህያ ዕጣ ፈንታ ይደርስባት እንደነበር ከነገረቻት በኋላ፣

"ለካስ የእኔ በሜዳ አህያ መረገጥ ለጥሩ ነገር ኖሯል! ጠጥዬ! በድዬሻለሁና ይቅርታ አድርጊልኝ፡፡ ከሜዳ አህያ ጀርባ ላይ ባልወረውርሽ ኖሮ እግርሽ አይሰበርም ነበር፡፡" ብላ ቀበሮ ጠጣን ይቅርታ ጠየቀቻት፡፡






"እኔ ይቅርታ አድርጌልሻለሁ፡፡ አንቺም ይቅርታ አድርጊልኝ፡፡ እግሬ ተሰብሮ በነበረበት ሰዓት ለእኔ አዝነሽ አቅፈሽና ደግፈሽ ከሜዳ አህያ ጀርባ ላይ አስቀመጥሽኝ፡፡ እኔ ግን ጨካኝ በመሆኔ እንደዚያ ተጐድተሽ እያየሁ ትቼሽ ሄድኩ፡፡" አለቻት፡፡

"እኔም ይቅር ብዬሻለሁ፡፡"

"አንዱ በሌላው ላይ በደል ቢያደርስበት ዞሮ ዞሮ በራሱ ላይ መድረሱ አይቀሬ ነው፡፡ ሁላችንም የሥራችንን ዋጋ አግኝተናል፡፡ ስለዚህ ከአሁን በኋላ ተዛዝነንና ተሳስበን መኖር አለብን፡፡" ብለው ወሰኑ፡፡ እርስ በርስ ተደጋግፈውም ወደ መጡበት ሥፍራ ተመለሱ፡፡



## ጥያቄ

1. ቀበሮ፣ ጦጣና የሜዳ አህያ ለምን ራቅ ወደ አለ ሥፍራ ለመሄድ ፈለጉ?
2. ጦጣ ለምን እግሯ ተሰበረ?
3. ቀበሮ ለምን በሜዳ አህያ ተረገጠች?
4. አንበሳ ማንን አሳደደ?
5. ጦጣና ቀበሮ ለምን ይቅርታ ተጠያየቁ?